ADDIS ABABA ETHIOPIA

በአዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ የዩናይትድ ስቴትስ ኤምባሲ የጥበብ ሥራዎች ስብስብ

ART COLLECTION OF THE UNITED STATES EMBASSY

ART COLLECTION OF THE UNITED STATES EMBASSY ADDIS ABABA ETHIOPIA

በአዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ የዩናይትድ
ስቴትስ ኤምባሲ የጥበብ ሥራዎች ስብስብ

CURATOR'S NOTE
Present Echoes

The art collection at the United States Embassy in Addis Ababa brings together works by 52 American and Ethiopian artists who explore how the past informs present circumstance, often through the lens of myth and memory. Many of the artists use the metaphor of nature to explore the human condition, while others draw on the immediacy of ordinary existence. Ranging from lyrical landscapes and representations of everyday life to bold and moody abstractions, the collection includes 100 works of contemporary art and encompasses paintings, sculptures, photographs, and works on paper.

For thousands of years, the cyclical patterns of change have stirred artistic inquiry and served as a means to understand the vicissitudes of civilization. The artists in the collection find evidence of transformation in the rich diversity of their respective country's land and inhabitants. They also highlight Ethiopia's contribution to the development of language and tools, and the importance of such everyday staples as coffee and bread. Travel and a love of homeland play significant roles as well, especially for Diaspora artists.

Whether social, archeological or geographic, the artworks on display chart fresh ways to forge cultural connections and imaginatively fill in the gaps between facts in the annals of history. Taking their cue from nature and personal experience, the artists each set out to restore balance and boldly express the resilience of the human spirit as the promise of a better future beckons.

Sarah Tanguy, Curator

የጥበብ ሥራዎች ጥርቅም ኃላፊ ማስታወሻ፡- የወቅቱ የገደል ማሚቶ

በአዲስ አበባ የዩናይትድ ስቴትስ ኤምባሲ የሥዕሎች ጥርቅም በ52 አሜሪካዊያን እና ኢትዮጵያውያን የተሠሩ የጥበብ ሥራዎችን ያካተተ ሲሆን፣ እነዚህ ሰዓሊያን የቀደመው ዘመን በአፈ-ታሪክ እና በትውስታ መስታወት በአሁኑ ጊዜ ያለው ነባራዊ ሁኔታ እንዴት እንደሚገለጽ በጥበብ ያሳዩናል፡፡ አብዛኞቹ አርቲስቶች የተፈጥሮን ቅኔያዊ ገጽታ በመጠቀም የሰውን ልጅ የአኗኗር ሁኔታ ሲዳስሱ፣ ሌሎቹ ደግሞ በመደበኛነት የሚታዩ ነገሮችን በጥበብ ሥራቸው በቀጥታ ይገልጻሉ፡፡ ጥልቅ ስሜትን ከሚያንጸባርቁ የተፈጥሯዊ የምድር አቀማመጥ እና የእለት ተለት የኑሮ እንቅስቃሴን የሚያስቃኙ ሥዕሎች በድምቀት እስከሚታዩ እና የስሜት መዋዠቅን የያዙ ረቂቅ የጥበብ ሥራዎች የሚገኙበት የሥዕሎች ጥርቅም 100 በዘመናዊ የሥዕል አሳሳል ጥበብ የተከናወኑ ስራዎችን እና የስዕል ቅቦችን፣ ቅርጻቅርጾችን፣ ፎቶግራፎችን እንዲሁም የወረቀት ላይ ሥራዎችን ያካተተ ነው፡፡

በሺዎች ለሚቆጠሩ አመታት የተካሄዱ ዑደታዊ ለውጦች ሥነ-ጥበባዊ አስተውሎትን ከማነቃቃቱም ባሻገር የሰው ልጅ ስልጣኔ ያስከተላቸውን አዳዲስ ክስተቶች ለመረዳት እንደ አንድ ዘዴ አገልግሏል፡፡ በጥርቅሙ ውስጥ የተካተቱት ሰዓሊያን በየአገራቸው መሬት እና ነዋሪዎች ዘንድ ባሉት እጅግ የከበሩ ልዩነቶች ላይ ለተካሄዱት የመለወጥ ሂደቶች ማስረጃ ሊሆኑ የሚችሉ የጥበብ ስራዎች አበርክተዋል፡፡ ከዚህም ሌላ ኢትዮጵያ ለቋንቋ እና ለመገልገያ መሣሪያዎች እድገት ያደረገችውን አስተዋጽዖ እና እንደ ቡና እና ዳቦ ያሉ የእለት ተእለት ፍጆታዎች ያላቸውን አስፈላጊነት በድምቀት ያሳያሉ፡፡ በተለይም በውጭ አገር ነዋሪ ለሆኑ ሰዓሊያን ጉዞ እና የትውልድ አገር ፍቅር ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡

የሥዕል ሥራዎቹ ማሕበራዊ፣ የከርሰምድር ወይም የመልከዓምድር ነጸብራቆች ቢሆኑም፣ የባሕል ትስስሮችን ለማጎልበት የሚያስችሉ አዳዲስ ዘዴዎች እና በእውነታዎች እና በታሪክ ድርሳናት መካከል ያለውንም ክፍተት በምናባዊ እሳቤ የሚሸፍኑ ናቸው፡፡ ተፈጥሮን እና የግል የሕይወት ልምዶቻቸውን እንደመፍትሔ አመላካች በመጠቀም ሰዓሊያኑ በጥበብ ሥራዎቻቸው ሚዛናዊነትን ለማስመለስ እና የሰው ልጅ የመንፈስ ጥንካሬ የፊታችን የተሻለ ጊዜ ተስፋ ሰጪ ስንቅ መሆኑን ለማሳየት ይተጋሉ፡፡

ሳራ ታንጋይ የጥበብ ሥራዎች ጥርቅም ኃላፊ

DAWIT ABEBE ዳዊት አበበ

Dawit Abebe's paintings feature dream-like images of life in a space beyond earth. Fantasy worlds are often painted with fluorescent colors on a background collage of newspaper print. Dawit grew up in Ethiopia and graduated from the Addis Ababa School of Fine Arts and Design. He also studied at the Surikov Fine Arts Institute in Moscow before becoming a teacher at the Addis Ababa School of Fine Arts and Design. He has exhibited his work in Ethiopia, the U.S. and Europe.

የዳዊት አበበ ሥዕሎች ከምድር ውጭ ባለ ስፍራ ሕልም መሰል የሕይወት ገጽታን ያሳያሉ፡፡ የምናብ አለማት ስዕሎች በአብዛኛው የሚሰሩት በፍሎረሰንት ቀለማት ሆኖ፣ በጋዜጣ ሕትመት ወረቀት ላይ ነው፡፡ ዳዊት በኢትዮጵያ ያደገ ሲሆን፣ ከአዲስ አበባ የሥነ-ጥበብ እና ዲዛይን ትምሕርት ቤት ተመረቀ፡፡ በአዲስ አበባ የሥነ-ጥበብ እና ዲዛይን ትምሕርት ቤት መምሕር ከመሆኑ በፊት በሞስኮ በሚገኘው ሱሪኮቭ የሥነ-ጥበብ ተቋም ተምሯል፡፡ የሥዕል ስራዎቹን በኢትዮጵያ፣ በዩናይትድ ስቴትስ እና በአውሮፓ ለዕይታ አቅርቧል፡፡

"Life brings a lot of inspiration for art. As well, dreams bring you a lot of ideas. Mainly I paint with my subconscious…but keeping in mind positive ideas, (through) which you can pass a lot of messages."

"ሕይወት ለጥበብ ሥራ ትልቅ መነሳሳትን ታበረክታለች፡፡ አንዲሁም፣ ሕልሞች በርካታ ሃሳቦችን ያበረክታሉ፡ ፡ በዋናነት የሥዕል ሥራዎቼን የምሰራው ጥልቅ በሆነው ልቦና ላይ በመመሥረት ነው …. ሆኖም ግን በርካታ መልዕክቶች ማስተላለፍ የሚቻልባቸውን አዎንታዊ አሳቢዎች በአዕምሮዬ አይዘለሁ፡፡"

KERIMA AHMED ከሪማ አሕመድ

Ethiopian artist Kerima Ahmed paints forms from life, creating emotive compositions that reflect common feelings such as contentment and sadness, as well as global concerns such as climate change. For Kerima, the ancient city of Harar is a "living art piece," and the colors and patterns found in homes and the traditional clothes seen in the markets have inspired many of her paintings. Kerima received a painting degree from the Addis Ababa Fine Arts School and a degree in Ethiopian language and literature at Addis Ababa University. She has exhibited her work in galleries, museums, embassies and cultural centers, and has worked with organizations to advance awareness of environmental issues through art.

ኢትዮጵያዊቷ አርቲስት ከሪማ አሕመድ የተለመዱ እና ጥልቅ ስሜት የሚጭሩ ሥዕሎች የምትስል ሲሆን፣ በጥበብ ሥራዎቿ ከሚንጸባረቁ ስሜቶች መካከል እርካታ እና ሐዘን ይካተታሉ፤ እንዲሁም በዓለም ዓቀፍ ደረጃ አሳሳቢ የሆኑ ለምሳሌ እንደ የአየር ንብረት ለውጥ የመሳሰሉትን በሥዕል ትገልጻለች፡ ፡ ለከሪማ፣ ጥንታዊቷ የሐረር ከተማ "ሕያው የሥነ-ጥበብ ውጤት" ናት፡፡ የአብዛኛዎቹ ሥዕሎቿ ቀለማት እና አጣጣል በከተማይቱ ቤቶች እና በገበያዎች አካባቢ በሚታዩት ባሕላዊ አልባሳት የተቃኙ ናቸው፡፡ ከሪማ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሥነ-ጥበብ ትምሕርት ቤት በስዕል ቅብ የመጀመሪያ ዲግሪ እንዲሁም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ቋንቋ ጥናት እና ሥነ-ጽሁፍ የመጀመሪያ ዲግሪ አግኝታለች፡፡ የሥዕል ሥራዎቿን በሰገነቶች፣ በቤተ መዘክሮች፣ በኢምባሲዎች እና በባሕል ማዕከላት አቅርባለች፤ በሥነ-ጥበብ አማካኝነትም በአካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ ያለውን ግንዛቤ በይበልጥ ለማሻሻል ሰርታለች፡፡

"Art is something that is not bound by geography or language. It is a global language. You can pick up an issue and share it with everyone… you can communicate and create understanding."

"ሥነ-ጥበብ በመልክዓምድር ወይም በቋንቋ የተገደበ ነገር አይደለም፡፡ ይልቁንም ዓለም ዓቀፋዊ ቋንቋ ነው፡፡ አንድን ርዕስ አንስተህ ከሰዎች ሁሉ ጋር ልትጋራው ትችላለህ…. የሃሳብ ግንኙነትን እና ግንዛቤን ልትፈጥር ትችላለህ፡፡"

CYNTHIA ALDERDICE ሲንቲያ አልዴርዳይስ

The Center of the Kingdom reflects Cynthia Alderdice's mastery of relief-process printing and innovations she has developed for her woodblocks, including techniques that achieve a smooth, painterly effect in her work. In printmaking and paintings, Alderdice explores life's larger significance and incorporates influences from her travels, including the art, design and mystical heritage of Tibet. A graduate of the University of Texas, Alderdice has work in collections including the Musee d'Art Contemporain, Chamalieres, France; the Robert C. Williams American Museum of Papermaking, Atlanta, Georgia; and the Baltimore Museum of Art, Baltimore, Maryland.

የግዛቱ እንብርት የተሰኘው የሲንቲያ አልዴርዳይስ ሥዕል የእፎይታ-ሂደት የተባለውን የሕትመት ጥበብ ምን ያህል እንደተጠበበችበት የሚያሳይ ነው፡፡ የተሳካ ሕትመት እና ፈጠራ የታከሉበት በእንጨት ቅርጽ የማውጣት ሥራ በዚህ የጥበብ ክንውን ላይ የሚታዩ ናቸው፡፡ በሕትመት እና በቀለም ቅብ ሥራዎቿ፣ አልዴርዳይስ የሕይወትን የላቀ ትርጉም ለመፈተሽ እና በጉዞዎቿ ያገኘቻቸውን ልምዶች ለማካተት ትጥራለች፡፡ በዚህም ውስጥ የቲቤት ሥነ ጥበብ፣ ንድፍ እና መንፈሳዊ ቅርስ ይንጸባረቃሉ፡፡ አልዴርዳይስ ከቴክሳስ ዩኒቨርሲቲ የተመረቀች ስትሆን በፈረንሳይ ለሙሲ ደ አርት ኮንተፖሬን (ቻማሊሬስ (Chamalieres)፣ በአትላንታ ጆርጂያ ለዘ ሮበርት ሲ. ዊሊያምስ የአሜሪካ ፔፐርሜኪንግ ቤተመዘክር፤ በባልቲሞር፣ ሜሪላንድ ባልቲሞር ቤተመዘክር ጭምር የሥራዋ ጥርቅሞች ይገኛሉ፡፡

Photographer Andargé Asfaw came to the U.S. as a teenager, attended high school in Ithaca, New York, and planned to return to Ethiopia. The military junta in 1974 changed his plans, but he has remained dedicated to his home country and its preservation. Andargé is the founder of Canopy Ethiopia, a non-profit organization dedicated to promoting sustainability in Ethiopia, and he is the author of *Ethiopia from the Heart*, a collection of images of Ethiopia's natural landscapes. Andargé attended Cornell University in Ithaca, New York, and is a graduate of the Hallmark Institute of Photography, Turners Falls, Massachusetts.

የፎቶግራፍ ባለሙያ የሆነው አንዳርጌ አስፋው በልጅነት ዘመኑ ወደ አሜሪካ መጣ፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምሕርቱን በኢታካ፣ ኒው ዮርክ ተከታተለ፡፡ ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ እቅድ ነበረው፡፡ በ1966 ስልጣን ላይ የወጣው የወታደሮች ቡድን እቅዱን እንዲለውጥ አደረገው፡፡ ሆኖም ግን ለትውልድ ሐገሩ እና ለዘላቂነቷም ያለው ቁርጠኝነት በጥብቅ ቀጥሏል፡፡ አንዳርጌ፣ ኢትዮጵያ ጥላ ከለላ የተባለውን ለአትራፊነት ያልተቋቋመ ድርጅት መስራች ሲሆን፣ በኢትዮጵያ ቀጣይ እድገት እንዲኖር የበኩሉን በቁርጠኝነት በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡ የኢትዮጵያን ተፈጥሯዊ የመሬት አቀማመጥ የሚያሳዩ ምስሎች ጥርቅም ያለበት *ኢትዮጵያ ከልብ* የተባለው መጽሐፍ ደራሲ ነው፡፡ አንዳርጌ በኢታካ፣ ኒው ዮርክ በሚገኘው ኮርኔል ዩኒቨርስቲ ትምሕርቱን ተከታትሎ በተርነርስ ፎልስ፣ ማሳቹሴትስ ከሚገኘው የሆልማርክ የፎተግራፍ ተቋም ምሩቅ ነው፡፡

"It is important for me to convey this work on handmade paper. An exciting new development is pulp-painting the color as an under-painting for the carved wood block on freshly made Kozo base sheet, thus creating a more dimensional and painterly look for the wood intaglio print."

"ይህንን ሥራ በእጅ በተሰራ ወረቀት ላይ ማሳየት ለእኔ ክፍ ያለ ዋጋ ያለው ነው፡፡ ቀለሙን በፐልፕ-ቅብ በስተጀርባ የቅለም ስብጥር በመፍጠር ተፍቆ በተዘጋጀ የእንጨት ማዕዘን፣ ላይ በኮዞ ንጣፍ በመጠቀም በርካታ ገጽታዎች ያሉት እና ቅቡም የሰመረ እንዲሆን ማድረግ በእውነቱ አስደሳች ሥራ ነው፡፡"

"I was travelling through the countryside in Tigray [province, Ethiopia] *and noticed children in the wheat fields late in the afternoon… As I took the photograph,* Running Through the Fields, *the children began running to see who I was. A watchful sibling stands by to monitor the situation."*

"[በኢትዮጵያ] የትግራይ [ክፍለ ሃገር] ስጓዝ ከቀትር በኋላ በስንዴ ማሳ ላይ ሕጻናትን አየሁ….. የመስኩን ፎቶግራፍ በማንሳት ላይ ሳለሁ ሕጻናቱ ማን እንደሆንኩ ለማየት ወደ እኔ መሮጥ ጀመሩ፡፡ የሕጻናቱ ንቁ ወንድም ሁኔታውን ለመከታተል ከጎኔ ቆመ፡፡"

ANDARGÉ ASFAW አንዳርጌ አስፋው

ELIZABETH ATNAFU ኤልሳቤጥ አጥናፉ

Elizabeth Atnafu's paintings explore the history and heritage of Africa and incorporate imagery from Latin America, a cultural influence she experienced living among the Latin American diaspora in New York City. Elizabeth was raised in Addis Ababa and came to the United States with her family when she was 14. She studied art at Howard University, Washington, D.C., where she received a bachelor of fine arts and a master of fine arts. Her work has been featured in individual and group exhibitions in the U.S., Europe and Africa and is represented in collections including the Paris Museum of Prints and Photography and the Museum of Modern Art in Mexico City, Mexico.

የኤልሳቤጥ አጥናፉ የሥዕል ቅቦች በአፍሪካ ታሪክ እና ቅርስ ላይ የሚያጠነጥኑ ናቸው፡፡ በኒው ዮርክ ከተማ ከላቲን አሜሪካ ከመጡ ሰዎች ጋር በመኖሯ ሳቢያ የእነርሱን ባሕል በሥዕሎቿ ላይ ታንጸባርቃለች፡፡ ኤልሳቤጥ ያደገችው በአዲስ አበባ ሲሆን፣ በ14 ዓመቷ ከቤተሰቧ ጋር ወደ አሜሪካ መጣች፡፡ በዋሽንግተን ዲሲ በሚገኘው ሆዋርድ ዩኒቨርሲቲ የሥነ-ጥበብ ትምሕርት ተከታትላለች፡፡ በዚያም የሥነ-ጥበብ የመጀመሪያ እና የድሕረ ምረቃ ዲግሪ አግኝታለች፡፡ የሥዕል ሥራዎቿም በግል እና በቡድን የኤግዚቢሽን ዝግጅቶች በአሜሪካ፣ በአውሮፓ እና በአፍሪካ ለዕይታ ቀርበዋል፡
፡ በፓሪስ ሙዚየም አፍ ፕሪንትስ ኤንድ ፎቶግራፊ ቤተ መዘክር እና በሜክሲኮ ሲቲ፣ ሜክሲኮ በሚገኘው ዘመናዊ የሥነ-ጥበብ ቤተመዘክር ውስጥ ባሉ የሥዕል ጥርቅሞችም ዘንድ የእርሷም የጥበብ ሥራዎች ይገኙባቸዋል፡፡

"When I came here (to the U.S.), there was a culture change for my family, but I didn't see much difference in my art. I respond to my own environment. The best part of (my work) is to communicate my individual way of expressing what I'm feeling."

"ዝዚህ ስመጣ (ወደ አሜሪካ)፣ ለቤተሰቤ የባሕል ለውጥ ነበር፣ በእኔ የሥዕል ሥራዎች ላይ ግን ብዙም ለውጥ አላየሁም፡፡ ሥራዎቼ ባለሁበት አካባቢ ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡ (የሥራዬ) እጅግ መልካም የሆነው ነገር፣ በግሌ በሚሰማኝ መንገድ ለሌሎች መግለጽ መቻሌ ነው፡፡"

MERIKOKEB BERHANU መሪኮከብ ብርሃኑ

Ripened fruits, blooming flowers, animals and female wombs are reoccurring themes in Merikokeb Berhanu's work, which is patterned and layered with bold, organic colors and forms. Merikokeb grew up in Ethiopia, attended the Addis Ababa School of Fine Arts and Design, and now paints at the Nubia Art Studio, a cooperative gallery near Addis Ababa. She has exhibited in Addis Ababa at the Russian Cultural Institute, Alliance Ethio-Francaise, Italian Cultural Institute, Makush Art Gallery, National Museum, Bulgarian Embassy, and the Hilton Hotel, as well as in galleries in Sudan and Djibouti.

የበሰሉ ፍሬዎች፣ በማበብ ላይ ያሉ አበቦች፣ እንስሳት እና የሴቶች ማሕጸን በመሪኮከብ ሥዕሎች ላይ በተደጋጋሚ ይታያሉ፡፡ ሥዕሎቹም በደማቅ፣ ተፈጥሯዊ ቀለማት እና ገፅታዎች የተሰሩ ናቸው፡፡ መሪኮከብ በኢትዮጵያ አደገች፡
፡ በአዲስ አበባ የሥነ-ጥበብ እና ዲዛይን ትምሕርት ቤት ትምሕርቷን ተከታትላ፣ በአሁኑ ወቅት በሕብረት ሥራ ማሕበር መልክ በተቋቋመው እና በአዲስ አበባ አቅራቢያ በሚገኘው በኑቢያ የሥነ-ጥበብ ስቱዲዮ የሥዕል ሥራዎች በመስራት ላይ ትገኛለች፡፡ የሥዕል ስራዎቿን በሩሲያ የባሕል ማዕከል፣ አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሴስ (Alliance Ethio-Francaise)፣ የጣሊያን የባሕል ኢንስቲትዩት፣ በማኩሽ የአርት ሠገነት፣ በብሔራዊ ቤተ-መዘክር፣ በቡልጋሪያ ኤምባሲ እና በሒልተን ሆቴል እንዲሆም በሱዳን እና በጅቡቲ በሚገኙ የሥዕል ሠገነቶች ለዕይታ አቅርባለች፡፡

"The life that we are passing, the complications, the density and the crowd, the thick fog and the smoke, the happiness and the hope entice me and cause the inner section that leads to my art."

"የምንኖረው ሕይወት፣ በውስጡ ያሉት ውስብስብ ነገሮች፣ አጣ ፈንታችን እና ሕዝቡ፣ ጥቅጥቅ ጭጋግ እና ጭስ፣ ደስታ እና ተስፋ የመነሳሳቴ ምክንያት ናቸው፤ እነርሱም ለሥዕል ሥራዎቼ ምሪትን ይሰጡኛል፡፡"

MICKAËL BETHE-SELASSIÉ ሚካኤል ቤተ-ሥላሴ

Mickaël Bethe-Selassié was born in Ethiopia and graduated from the Lycee Guebre Maryam in Addis Ababa before moving to France. Though he studied science at university, Mickaël discovered a latent artistic ambition when he was redecorating his small Paris apartment. The self-taught artist started with clay and moved to papier-mâché to construct his bold, animated sculptures. Mickaël's work has been in individual exhibitions in Brazil, Namibia, South Africa and Europe, as well as group shows throughout the U.S. and Europe.

ሚካኤል ቤተ-ሥላሴ በኢትዮጵያ ተወለደ፡፡ ወደ ፈረንሳይ ተጉዞ በቋሚነት ኑሮውን ከመመሥረቱ በፊት በአዲስ አበባ በሚገኘው ሊሴ ገብረ ማሪያም ትምሕርት ቤት ትምህርቱን አጠናቀቀ፡፡ የትምሕርት መስኩ ሳይንስ ቢሆንም እንኳን፣ በፓሪስ የሚገኘውን አነስተኛ አፓርታማውን በማስዋብ ላይ በነበረ ጊዜ የሥዕል ችሎታ በውስጡ እንዳለ ተገነዘበ፡፡ ራሱን በራሱ ያስተማረው ይህ አርቲስት በመጀመሪያ በሸክላ አፈር ከዚያም በፔፐር-ሜሽ ደማቅ እና ጥበብ የተሞላባቸውን የቅርጻ ቅርጽ ስራውን መሥራት ጀመረ፡፡ የሚካኤል ሥራዎች በብራዚል፣ በናሚቢያ፣ በደቡብ አፍሪካ እና በአውሮፓ የግል ኤግዚቢሽኖች እንዲሁም በመላው አሜሪካ እና አውሮፓ የቡድን ትዕይንቶች ለዕይታ ቀርበዋል፡፡

"The noise and the smell of Addis Ababa accompanied the creation of the armatures (for Sentinel *and* Totem*)….as well as the papier-mâché that is made entirely from local newspapers soaked in water and then kneaded. The chair is the skeleton and the papier-mâché is the flesh of these creations that, dressed in hot colors, exude a scent of mystery. My work represents a personal universe that I dreamed."*

"የአዲስ አበባ ድምጽ እና ሽታ በቅርፃ ቅርፆች ማዕቀፎች ውስጥ (ለጥበቃዎች እና አርማዎች) ይካተታሉ .... በተጨማሪም ሙሉ በሙሉ በውሃ ውስጥ በተነከሩ እና በላቆጡ የጋዜጣ ወረቀቶች የተሰሩ ናቸው፡፡ ወንበሩ የተሠራበት ቅርፀ መዋቅር ሲሆን ፔፐር-ሜሽ ደግሞ የቅርው አካል ነው፡፡ ይህም ደመቅ ባሉ ቀለሞች የተሰራ ነው፡፡ ይህም ሚስጢራዊነትን የሚያንፀባርቅ ነው፡፡ ይህ ስራ በግሌ ያለምኩትን አለም ይወክላል፣ ያመለክታል፡፡"

BEHAILU BEZABIH በሐይሉ በዛብሕ

Behailu Bezabih's subject matter is the chaotic urban environments of African and European cities, and often includes carnival-style images of the cars, vans, bicycles and buses that define and congest the urban landscape. He draws his greatest inspiration from the children he teaches at the Bethal Mekane Yesus mission school and their uninhibited, artistic mode of expression. Behailu is one of a small group of Ethiopian artists who live and work in Addis Ababa and have travelled and held residencies abroad.

የበሐይሉ በዛብሕ የሥዕል ሥራዎች ዋነኛ ርዕስ በአፍሪካ እና በአውሮፓ ከተሞች ያለው የትርምስ ሕይወት ነው፡ ፡ ብዙውን ጊዜ በሥዕል ሥራዎቹ ውስጥ የከተማን ገፀ-ምድር የሚያጨናንቁ ተሽከርካሪዎች፣ የእቃ መጫኛዎች፣ ብስክሌቶች እና አውቶብሶች ይካተታሉ፡፡ እነዚህም በከተሞች አካባቢ ያለውን ሁኔታ ያሳያሉ፡፡ ከፍተኛ መበረታታትን የሚያገኘውም በቤተል መካነ ኢየሱስ ሚሲዮን ትምሕርት ቤት ከሚያስተምራቸው ሕጻናት እና ከእነርሱም ነጻ እና ጥበብ የተሞላበት ራስን የመግለጽ ችሎታ ነው፡፡ በሐይሉ በአዲስ አበባ ከሚኖሩ እና ከሚሰሩ እንዲሁም ወደ ውጭ ሃገራት ከተጓዙ እና በዚያም በቋሚነት ከሚኖሩ ጥቂት የኢትዮጵያውያን የሥነ-ጥበብ ሰዎች መካከል አንዱ ነው፡፡

"In the beginning of my career I painted naturalistically, the way I was taught at school. Later, I learned that it was not the only way, and my approach to painting changed gradually. Since I am a school art teacher, the works of my students have influenced or inspired me. Through time, I have developed a certain style that I let grow in me and follow its own course."

"በሙያዬ የመጀመሪያ ጊዜያት በትምሕርት ቤት እንደተማርኩት ሁሉ በተፈጥሮ ላይ በማተኮር እስል ነበር፡፡ በኋላ የሥዕል ጥበብ በአንድ መንገድ ብቻ እንደማይጓዝ ተረዳሁ፤ ቀስ በቀስም የአሳሳል ዘይቤዬ ተለወጠ፡፡ በትምሕርት ቤት የማስተምር የሥዕል መምሕር እንደመሆኔ መጠን፣ የተማሪዎቼ የሥዕል ሥራዎች በእኔ ላይ አዎንታዊ ተጽእኖ እና መነቃቃትን አስከትለዋል፡፡ በሂደትም፣ በውስጤ አንዳች የተለየ የአሳሳል ዘይቤ እንዲያድግ ፈቀድኩ፤ የራሱንም ተፈጥሯዊ ሂደት ተከትሎ እንዲያድግ አደረግሁ፡፡"

CRAIG CAHOON ክሬግ ካሁን

Craig Cahoon has always been interested in the archetypal images and histories of other countries and cultures. He travelled the world to experience the art, architecture and cultural sensibilities that now inform his artwork. *Bee* references the bee's sacred status in ancient Near East and Aegean cultures, in this case the Bee Goddess from Greek mythology adorned with a butterfly above her head and flanked by winged dogs. Cahoon's work has been shown in solo and group exhibitions and is featured in numerous private and public collections.

ክሬግ ካሁን ሁሌም ቢሆን የመጀመሪያ ለሆኑ ምስሎች እና የሌሎች ሀገራት ታሪኮች እና ባህሎች ልዩ ዋጋ ይሰጣል፡ ፡ ስነጥበብን፣ ስነ ህንፃን እና ባህልን ለማወቅ በአለም ዙሪያ የተጓዘ ሲሆን ከዚህም ያገኘው ልምድ በጥበብ ስራዎቹ ላይ ዋነኛ ግብዓቶች ናቸው፡፡ ንብ በጥንታዊቷ ቅርብ ምስራቅ እና በኤጂያን (Aegean) ባህሎች ውስጥ የነበራትን ከፍተኛ ቅዱስ ስፍራ የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህም ረገድ በግሪክ የአፈታሪክ እምነት የንብ አምላክ በጭንቅላቷ አካባቢ በቢራቢሮዎች ደምቃና ክንፍ ባላቸው ውሾች ታጅባ ትታያለች፡፡ የካሁን ስራ በግል እና በቡድን ኤግዚብሽኖች ለእይታ የቀረቡ ሲሆን በበርካታ የግል እና/ወይም የጥበብ ስራ ጥርቅሞች ታይተዋል፡፡

"I employ figuration to represent personal episodes in my life, using imagery from different cultures as well as my own dreams. Sometimes the figurative elements evolve into more abstract imagery. Although rooted in representational figurative painting, abstraction allows me to paint more what I am feeling rather than realistically reproducing what I am seeing."

"በህይወቴ ውስጥ የማያቸውን ነገሮች በጥበብ መግለፅ አዘወትራለሁ፡፡ ከተለያዩ ባህሎች እና በራሴም ከማልማቸው ነገሮች በመነሳት እዝህን በጥበብ አገልግለሁ፡፡ አንዳንድ ጊዜ እዝህ ወካይ የጥበብ ስራዎች በይበልጥ አብስትራክት ይሆናሉ፡፡ በአርግጥ በአለም ላይ የማያቸውን ነገሮች በስዕል አማካይነት ወክዬ ለማቅረብ ጥረት ባደርግም ረቂቅ በሆነ የአሳሳል ዘዴ በተጨባጭ ከማያቸው ነገሮች ይልቅ ስሜቴን ለመግለፅ ያስችለኛል"



JERRY CLAPSADDLE ጄሪ ክላፕሳዲል

Jerry Clapsaddle explores order and chaos in the lines, forms and shapes of geometric pattern generation. *Squall* and other work reflect the stylistic features of Pattern Painting from the 1970s, a movement that sought to bridge the gap between folk art and high art. Born in Hastings, Nebraska, Clapsaddle studied art and graphic design at Indiana University. As an art professor at George Mason University in Fairfax, Virginia, he worked to promote student and faculty art by creating opportunities for public exhibitions. He has exhibited at P.S. 1 Gallery, New York City; Project Studios One, Long Island City, New York; and at the Museum of Modern Art, Oxford, U.K.

ጄሪ ክላፕሳድል ፎርሞችን እና የጂአሜትሪ ቅርፆችን በመጠቀም ስርዓትን እና ውጥንቅጥ ሁኔታ የተመላበትን ነባራዊ አቀማመጥ በጥበብ ስራ ያሳያል፡፡ ምንድ እና ሌሎች ስራዎቹ በ1970ዎቹ የነበሩትን የስዕል አሳሳል ዘይቤዎች አካተዋል፡፡ የዚህም አላማ በጥንት ዘመን የነበረውን የጥበብ ስራ በአሁኑ ወቅት ካለው ከፍተኛ ደረጃ የጥበብ ስራ ጋር ያለውን ልዩነት ለማጥበብ ነው፡፡ ጄሪ ክላፕሳድል በህስቲንግስ፣ ኔብራስካ ተወልዶ በኢንዲያና ዩኒቨርስቲ ሥነ-ጥበብ እና ግራፊክ ዲዛይን ተማረ፡፡ በፌር ፋክስ፣ ቨርጂኒያ በጆርጅ ሜሰን ዩኒቨርስቲ የሥነ-ጥበብ ፕሮፌሰር ነው፡፡ ህዝባዊ ኤግዚብሽን በማዘጋጀት የተማሪዎች እና የፋኩልቲ ሥነ ጥበብን ለማበረታታት ሲሰራ ቆይቷል፡፡ በኒው ዮርክ ከተማ በፒኤስ ፣ ሠገነት በፕሮጀክት ስቱዲዮስ ዋን ስራዎቹን አቅርቧል፡፡ ከዚህም ባሻገር በሎንግ አይላንድ ከተማ፣ ኒው ዮርክ እና በኦክስፎርድ፣ ዩናይትድ ኪንግደም የዘመናዊ ሥነ ጥበብ ቤተ መዘክር የስዕል ስራዎቹን አቅርቧል፡፡

STEVEN CUSHNER ስቲቨን ኩሽነር

Steven Cushner's work has ranged from oils on oversized canvases to watercolors the size of a credit card. His geometric art often refers to aspects of daily life, and frequently includes paint drips breaking form through bold, color-drenched patterns. Cushner was born in Cleveland, Ohio, and earned a bachelor of fine arts at the Rhode Island School of Design and a master of fine arts at the University of Maryland. He has been on the teaching staff of several universities and has had numerous group and one-person shows. He is represented in the collections of the U.S. Library of Congress, Washington, D.C.; the Aspen Institute, Washington, D.C.; and The Hirshhorn Museum and Sculpture Garden, Washington, D.C.

የስቲቨን ኩሽነር ሥራዎች በትልልቅ ሸራዎች ላይ ከተሰሩ ባለ ዘይት ቀለም ስዕሎች አንስቶ በውሃ ቀለም እስከተሰሩ የክሬዲት ካርድ መጠን ያላቸው ናቸው፡፡ በጂአሜትሪክ አሰራር የሚሰራቸው ስዕሎች የየዕለት ህይወትን የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡ ብዙውን ጊዜ ስዕሎቹ በደማቅ ቀለማት የተሰሩ ናቸው፡፡ ኩሽነር የተወለደው በክሌቭላንድ፣ አሃዮ ነው፡፡ ከሮድ አይላንድ ስኩል አፍ ዲዛይን በሥነ-ጥበብ የመጀመሪያ ዲግሪ፣ ከሜሪላንድ ዩኒቨርስቲ የሥነ-ጥበብ የድህረ ምረቃ ዲግሪ አግኝቷል፡፡ በበርካታ ዩኒቨርስቲዎች በመምህርነት ያገለገለ ሲሆን በብዙ የቡድንና ግላዊ ኤግዚብሽኖች ተሳትፏል፡፡ በአሜሪካ የኮንግረስ ቤተ መጽሐፍት፣ ዋሽንግተን ዲሲ ፣ በአስፔን ኢንስቲትዩት፣ ዋሽንግተን ዲሲ እና በሂርሾርን ቤተ መዘክር እና ስካልፕቸር ጋርደን፣ ዋሽንግተን ዲሲ ስራዎቹን ለእይታ አቅርቧል፡፡

"Painting… is an accumulation of all the mistakes, corrections, moves, and decisions that occur while trying to make a vision, a feeling, and an experience concrete."

"ሥዕል... አንድን ምስል፣ ስሜት አንዲሁም የህይወት ልምድ በተጨባጭ ለማስቀመጥ ለሚደረግ ጥረት ውስጥ የሚከማቹ ስህተቶችን፣ የአነርሱን ማስተካከያዎች፣ የአሳሳሉን ሂደት እና በዚያም ወቅት በሰዓሊው የሚወሰዱ ውሳኔዎችን ያካተተ ነው፡፡"

FRANK HALLAM DAY ፍራንክ ሃላም ዴይ

Frank Hallam Day's photographic work has often taken him to Africa, and in particular to Ethiopia. Before becoming a full-time artisit, he worked for the U.S. State Department, and travelled to Ethiopia repeatedly. He studied Social Sciences at the University of Chicago and earned a master's degree in Sociology at the University of California at Santa Barbara, an academic background evident in his focus on the social context and cultural background of his subjects. Day has won numerous awards and international recognitions for his work, which is represented in museum and private collections worldwide. His photographs are in the collections of the State Museum of Berlin, the Baltimore Museum of Art, the Portland Art Museum, the San Diego Museum of Photographic Arts, the Corcoran Gallery of Art, Washington, D.C., and several U.S. State Department Art in Embassies collections.

የፍራንክ ሃላም ዴይ የፎቶግራፍ ስራ ብዙውን ጊዜ ወደ አፍሪካ በተለይም ወደ ኢትዮጵያ እንዲጓዝ አድርጎታል፡ ፡ ሙሉ ጊዜውን ለጥበብ ሥራ ማዋል ከመጀመሩ በፊት በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይሰራ ስለነበረ በተደጋጋሚ ወደ ኢትዮጵያ ተጉዟል፡፡ በቺካጎ ዩኒቨርስቲ የማህበራዊ ሳይንስ ትምህርት ተከታትሏል፡፡ በሳንታ ባርባራ በሚገኘው የካሊፎርኒያ ዩኒቨርስቲ የህብረ-ሰብ ጥናት የድህረ ምረቃ ዲግሪ አግኝቷል፡፡ የተማራቸው ትምህርቶች በማህበራዊ ህይወት እንዲሁም ለባህል የሚሰጠውን ትኩረት የሚደግፉ ናቸው፡፡ ዴይ በስራዎቹ በርካታ ሽልማቶች እና ዓለም ዓቀፋዊ እውቅና አግኝቷል፡፡ በሥራዎቹም በአለም ዙሪያ በቤተ-መዘክር እና በግል ጥርቅሞች ውስጥ ተመልክቷል፡፡ ፎቶግራፎቹ በበርሊን ስቴት ቤተ-መዘክር፣ ባልቲሞር የስነ-ጥበብ ቤተ-መዘክር፣ ፖርትላንድ የስነ-ጥበብ ቤተ-መዘክር፣ ሳን ዲየጎ የፎቶግራፊክ ጥበብ ቤተ-መዘክር፣ ኮርኮራን የስነ-ጥበብ ሠገነት፣ ዋሽንግተን ዲሲ እና በተለያዩ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የኤምባሲዎች የጥበብ ስራዎች ጥርቅሞች ውስጥ ስራዎቹ ለእይታ ቀርበዋል፡፡

"Billy Dean is a portrait taken in the cloth and curtain market in Addis Ababa, and portrays a member of an ethnic group from the extreme western area of Ethiopia, an area of some ethnic tension. This image was featured as part of a portrait project on the Addis Ababa market, which was exhibited upon completion in the market itself."

"ቢሊ ዲን ከአዲስ አበባ የአልባሳት እና የመጋረጃዎች ገበያ የተወሰደ ፎቶግራፍ ሲሆን የሚያሳየውም ከኢትዮጵያ የምዕራብ ጫፍ አካባቢዎች የመጡ ብሔሮችን የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ የኢትዮጵያ ስፍራ ከብሔር ጋር በተያያዘ ውጥረት የሚታይበት ነው፡፡ ይህ ፎቶግራፍ የአዲስ አበባን ገበያ ያሳያል፡፡ ስራውም በተጠናቀቀ ጊዜ በገበያው ለእይታ ቀርቦ ነበር"

ELIZABETH DOVE ኤሊዛቤት ዶቭ

Elizabeth Dove's art is a quest for meaning explored through the mechanics of process and reassignment. Her prints, cutouts and installations are all consigned to missions: to suggest eternity and timelessness, or to observe how impermanence and stability interact. Dove is associate professor at the University of Montana where she teaches printmaking, photography, and courses integrating printmaking, photography and digital media. She has exhibited extensively throughout the U.S. and has been in shows in Japan, Ireland, Canada, and Scotland.

የኤልዛቤት ዶቭ የሥነ-ጥበብ ስራ በሂደት እና በመልሶ ማቀናጀት አማካይነት ትርጉም ለማግኘት የሚደረግን ጥረት ያሳያል፡፡ የሥዕል፣ የመቆራረጥ እና የመገጣጠም ሥራዎቿ አንድን ተልዕኮ ኢላማ ያደረጉ ናቸው፡- ይህም ማለት አጠቃላይነትን እና ጊዜ ማከበርን፣ ወይም መረጋጋትን ማጣት ከመረጋጋት ጋር ያለውን መስተጋብር ማሳየት ነው፡፡ ዶቭ በሞንታና ዩኒቨርስቲ ተባባሪ ፕሮፌሰር ስትሆን በዚያም ስለ ህትመት፣ የፎቶግራፍ ሙያ እና ከህትመት፣ ከፎቶግራፍ ሙያ እና ከዲጂታል ሚዲያ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ትምህርቶች ታስተምራለች፡፡ ስራዎቿም በመላው አሜሪካ በስፋት ለእይታ የቀረቡ ሲሆን በጃፓን፣ አየርላንድ፣ ካናዳ እና ስኮትላንድም ስራዎቿ ለምልከታ ቀርበዋል፡፡

"I establish a repetitive process in the making of the work: I cut up dictionaries letter by letter, I embroider with human hair, I transcribe the personal journals of others on my skin. These processes serve as a physical act of remembrance, and embody a somewhat ritualistic response to the passing of time where making an object first begins by unmaking another."

"ስራውን ለመስራት ተደጋጋሚ ሂደትን እከተላለሁ፥ መዝገበ ቃላትን ቃል በቃል አቆርጣለሁ፥ ይህንንም በሰው ልጅ ጸጉር አንደጥልፍ እሰራዋለሁ፥ የሌሎችን ግላዊ ማስታወሻዎችን በራሴ ቆዳ ላይ እጽፋለሁ፡፡ እነዚህ ሂደቶች ቁስ አካላዊ ትውስታን የሚያሳዩ ናቸው፥ ለሚያልፈውም ጊዜ በእውነት ላይ የተመሠረተ ምላሽ መስጠትን ያቀፉ ናቸው፡፡ በዚህም ረገድ አንድን ነገር መሥራት የሚጀመረው ሌላውን በመበታተን ይሆናል፡፡."



Melvin Edwards' art addresses his existence as an African-American as well as the oppression of African people in their native countries. The great, great-grandson of an African blacksmith brought to the United States as a slave, Edwards is renowned for his series *Lynch Fragments*, abstract, welded-metal sculptures inspired by the civil rights movement. Traveling on Fulbright scholarships, Edwards has conducted workshops on the art of metal sculpture for artists of Zimbabwe. A Texas native, he studied art and art history on the West Coast then moved to New York, where he lectures on contemporary art and teaches at the Mason Gross School of Arts, Rutgers University, New York City. He has received numerous commissions for his work.

የሜልቪን ኤድዋርድስ የጥበብ ሥራ የእርሱን አፍሪካዊ-አሜሪካዊነት የሚመለከት ነው፡፡ እንዲሁም አፍሪካዊያን ሕዝቦች በየትውልድ ሃገሮቻቸው የሚደርሱባቸውን ጭቆናዎች በጥበብ ሥራው ያሳያል፡፡ ኤድዋርድስ በባርነት ቀንበር ስር ወደ አሜሪካ የመጣ የአንድ አንጥረኛ የልጅ ልጅ፣ ልጅ እንደመሆኑ መጠን፣ ,ያለፍርድ ,ይፈጸሙ የነበሩ ግድያዎችን በተደጋጋሚ እና በከፊል በሚያሳዩ፣ ረቂቅ እና በተበየደ ብረት በተሰሩ ቅርጻ ቅርጾቹ በሰፊው ይታወቃል፡ ፡ የእነዚህም ሥራዎቹ ዋነኛ መነሻ የሰብዓዊ መብቶች ትግል ነው፡፡ በፉልብራይት ነጻ የትምሕርት እድል አማካኝነት ወደ ተለያዩ ሃገራት የተጓዘ እንደመሆኑ መጠን፣ ለዚምቧቤ አርቲስቶች ብረትን በመጠቀም ስለሚሰሩ የጥበብ ሥራዎች ትምህርት አካሂዷል፡፡ የተወለደው በቴክሳስ ሲሆን፣ በምዕራብ ጠረፍ ሥነ-ጥበብ እና የሥነ-ጥበብ ታሪክ ትምሕርት ተምሮ፣ ዘመናዊ የሥነ-ጥበብ ትምሕርት ወደሚያስተምርበት ኒው ዮርክ ተዛወረ፡፡ በተጨማሪም በኒው ዮርክ ከተማ በሚገኘው ሩትገርስ ዩኒቨርሲቲ ሜሰን ግሮስ ስኩል አፍ አርትስ በመምሕርነት ይሰራል፡፡ በዚህ ሥራውም ለበርካታ ኃላፊነቶች ለመብቃት ችሏል፡፡

"Abubi Light was one of my responses to my first visit to Africa in 1970. The dynamic of people and land in the sunlight on the hills between Kumasi and Accra in Ghana."

"ኣቡቢ ላይት በ1970 [ኤ.ኤ.] ለመጀመሪያ ጊዜ በአፍሪካ ካደረግሁት ጉብኝት ምላሾች መሀከል አንዱ ነው፡ ፡ በኩማሲ እና አክራ መካከል በሚገኘው አቀበቶች፥ በጸሃይ ብርሃን በደመቀው ስፍራ የሰዎችን እንቅስቃሴ እና የመሬቱን ሁኔታ ያሳያል፡፡"

MELVIN EDWARDS ሜልቪን ኤድዋርድስ

YOHANNES GEDAMU ዮሃንስ ገዳሙ

In Yohannes Gedamu's paintings we see color, form, texture and often figures, all expressions of creative, subjective and emotional ideas floating between the conscious and subconscious. After attending the Addis Ababa Fine Arts School, Yohannes lived abroad in Mombassa and Germany, and claims his years in Africa and Europe informed his palette and compositions. Yohannes returned to Ethiopia and helped create forums and roundtables for fellow artists, helping to engage and promote the country's artistic community.

በዮሃንስ ገዳሙ ሥዕሎች ቀለማትን፣ ወጥነትን፣ ቅርጽን እና በአብዛኛው ደግሞ ምስሎችን እናያለን፤ ሁሉም ፈጠራ የተሞላባቸው እና በንቁ ሕሊናችን እና በእዝነ ልቦናችን መካከል የሚንሳፈፉ ስሜቶችን እንመለከታለን፡፡ በአዲስ አበባ የሥነ-ጥበብ ትምሕርት ቤት ትምሕርቱን ካጠናቀቀ በኋላ፣ ዮሃንስ በሞምባሳ እና በጀርመን ኖሯል፤ በአፍሪካ እና በአውሮፓ የኖረባቸው ጊዜያት የሚጠቀምባቸው ቀለማት ባሕሪያት እና ውሕዶች መፍለቂያ መሆናቸውን ይገልጻል፡ ፡ ዮሃንስ ወደ ኢትዮጵያ በመመለስ ለአርቲስቶች የውይይት መድረኮችን እና የዙሪያ ክብ ጠረጴዛ ውይይቶችን በማቋቋም ረድቷል። የዚህም አላማ የሃገሪቱን የሥነ-ጥበብ ማሕበረሰብ ለማሰባሰብ እና ለማጠናከር ይረዳ ዘንድ ነው፡፡

"I am not illustrating or telling a story. There is no story behind it. The painting is rather out there only to incite different emotions from different people. That is why I don't give them titles."

"በሥዕል አማካኝነት አንድን ታሪክ እየተረከሁ ወይም እየገለጽኩ አይደለም፡፡ ከኋላው ምንም ታሪክ የለም፡፡ የሥነ-ጥበብ አላማ በተለያዩ ሰዎች ዘንድ የተለያዩ ስሜቶችን መጫር ነው፡፡ ለዚህ ነው ለሥዕሎቼ አርዕስትን የማልሰጠው፡፡"

TAMRAT GEZAHEGN ታምራት ገዛሄኝ

To emphasize process and spontaneity, Tamrat Gezahegn works with a variety of impermanent media, including recycled cardboard. His distinctive "of the moment" paintings are both abstract and representational, with signature brushstrokes, line and color. In recent paintings Tamrat transcribes poetic, cryptic passages, written in Amharic, from his personal journal onto cardboard, passages he describes as visual music for a journey through the layers of his thoughts. A studio artist, Tamrat lives and works in Addis Ababa. He graduated from Addis Ababa School of Fine Arts and Design and has had group and solo exhibitions in Ethiopia and Spain.

ለሂደት እና ለነገሮች በራሳቸው ጊዜ መከሰት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ታምራት ዝቺኝ በተለያዩ ቋሚነት በሌላቸው መሳሪያዎች በመጠቀም የሥዕል ሥራዎቹን ይሰራል፡፡ ወዲያውኑ በመጣለት ሐሳብ ላይ ተመሥርቶ የሚሰራቸው ሥዕሎች ረቂቅ እና ወካይ ሲሆኑ፣ የቀለም ብሩሽ የተዋቸው ምልክቶች በመስመሮች እና በቀለማት ተመልክተዋል፡፡ በቅርቡ በሰራቸው ሥዕሎች በግል ስብስቡ የሚገኙ ግጥም ነክ እና ምስጢራዊ የአማርኛ ጽሁፎች በጥበብ ተገልጸዋል፡ ፡ እነዚህን ጽሁፎች በሃሳቦቹ ክምችቶች ውስጥ ወደ አንዳች ስፍራ የሚወስዱ የእይታ ሙዚቃዎች ናቸው ይላቸዋል፡ ፡ በስቱዲዮ ሰዓሊ የሆነው ታምራት የሚኖረው እና የሚሰራውም አዲስ አበባ ውስጥ ነው፡፡ ከአዲስ አበባ የሥነ-ጥበብ እና ዲዛይን ትምሕርት ቤት ትምሕርቱን ያጠናቀቀው ታምራት፣ የሥዕል ሥራዎቹን በተናጠል እና በቡድን ኤግዚቢሽኖች በኢትዮጵያ እና በስፔን ለዕይታ አቅርቧል፡፡

PATRICIA C. GOSLEE ፓትሪሺያ ሲ. ጎስሊ



The painting *Subsequently Wind* reflects Patricia Goslee's interest in creating visual expressions of non-physical dimensions, such as energy fields and brain activity. Her work incorporates the colors associated with the energy centers of the body, or chakras, and explores the potential for healing and liberation from negative thought patterns. Born in San Diego, California, Goslee earned a bachelor of fine arts in graphic design from the University of Georgia and a master of fine arts in painting from Catholic University in Washington, D.C. Her art is in many public and private collections, including *The Washington Post*, Washington, D.C.; the National Institutes of Health, Bethesda, Maryland; and the U.S. Embassy in Nepal.

ተከታዩ ንፋስ የተሰኘው የሥዕል ሥራ ፓትሪሺያ ጎስሊ ቁስ አካላዊ ያልሆኑ ነገሮችን ለምሳሌ የኤነርጂ መስኮች እና የአዕምሮ ውስጣዊ አሰራርን በሥዕል የመግለጽ ጥልቅ ፍላጎት ያላት መሆኑን ያሳያል፡፡ በዚህ ሥራዋ ውስጥ ከሰውነታችን የሃይል ወይም የመንፈስ ብርታት ማዕከላት ጋር የተያያዙ ቀለማትን አካትታለች፡፡ አሉታዊ ከሆነ አስተሳሰብ እንዴት መፈወስ እና ነጻ መውጣት እንደሚቻል በሥዕሎቿ የመግለጽ ዘይቤን ትከተላለች፡፡ ጎስሊ የተወለደችው በሳን ዲዬጎ፣ ካሊፎርኒያ ሲሆን፣ ከጆርጂያ ዩኒቨርሲቲ (University of Georgia) በሥነ-ጥበብ እና በግራፊክ ዲዛይን የመጀመሪያ ዲግሪ እና በዋሽንግተን ዲ.ሲ. የካቶሊክ ዩኒቨርሲቲ በሥነ-ጥበብ የድሕረ ምረቃ ዲግሪዋን አግኝታለች፡፡ የሥዕል ስራዎቿ በበርካታ ሕዝባዊያን እና የግል ጥርቅሞች ዘንድ ይገኛሉ፤ ከነዚህም መካከል *ዘ ዋሽንግተን ፖስት*፣ ዋሽንግተን ዲ.ሲ. ፣ በቤቴስዳ፣ ሜሪላንድ በሚገኘው ብሔራዊ የጤና ተቋማት እና በኔፓል በሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ ይካተታሉ፡፡

"I am trying to consciously make works that radiate positive energy, or express a sense of hope—literal patterns that represent the experience of breaking through the restrictive filters of fear-based thought…."

"በልዩ ትኩረት፣ አዎንታዊ ሃይልን የሚፈነጥቁ ወይም ተስፋ የመሰነቅ ስሜትን የሚያጭሩ ስራዎች ለመስራት እሞክራለሁ፡- በዚህም መሰረት በፍርሃት ላይ የተመሠረቱ ሃሳቦች የሚያስከትሉትን አቃቢ ማጠንፈፊያዎች ሰብሮ መውጣትን የሚወክሉ መስመሮች እጠቀማለሁ…."

TEKLEMARIAM ZEWDE HABTEGIORGIS ተክለማሪያም ዘውዴ ሃብተጊዮርጊስ

Born in Addis Ababa, Teklemariam Zewde Habtegiorgis interprets images of Ethiopian culture in oil paintings, drawings, watercolors and mosaics. Growing up, Teklemariam knew he wanted to be an artist. He believes this early awareness allowed him to focus and improve his art skills from an early age. He graduated from Addis Ababa School of Fine Arts and Design and has exhibited his work in Addis Ababa, Djibouti, Geneva, Frankfurt, Vienna, Beijing, Philadelphia, Los Angeles, Washington, D.C., and New York.

ተክለማሪያም ዘውዴ ሃብተጊዮርጊስ በአዲስ አበባ የተወለደ ሲሆን የኢትዮጵያን የባህል ቅርጾች በዘይት ቀለማት፣ በስዕሎች፣ በውሃ ቀለማት እና በሞዛይክ አማካኝነት ይተረጉማል፡፡ ተክለማሪያም በእድገት ዘመኑ አርቲስት የመሆን ፍላጎት እንዳለው በሚገባ ያውቅ ነበር፡፡ በልጅነት ዘመኑ ይህንን ማወቁ ከመጀመሪያውም የሥዕል ክህሎቶቹ ላይ እንዲያተኩር እና እነርሱንም እንዲያሻሽል ረድቶታል፡ ፡ ከአዲስ አበባ የሥነ-ጥበብ እና የዲዛይን ትምሕርት ቤት የተመረቀ ሲሆን፣ በአዲስ አበባ፣ በጅቡቲ፣ በጄኔቫ፣ በፍራንክፈርት፣ በቤጂንግ፣ በፊላዴልፊያ፣ በሎስ አንጀለስ፣ በዋሽንግተን ዲ.ሲ.፣ እና በኒው ዮርክ የሥዕል ሥራዎቹን ለዕይታ አቅርቧል፡፡

DESTA HAGOS ደስታ ሃጎስ

Desta Hagos' scenes from everyday life in Ethiopia convey the struggles women face or feature men just contemplating life on a door stoop. Desta also paints still lifes, landscapes and abstract compositions. When she graduated from Addis Ababa Fine Arts School in 1969, Desta's graduation exhibition was Ethiopia's first one-person show of a woman artist. She also received a bachelor of fine arts from California Lutheran University, Thousand Oaks, California, where she won a full scholarship, and was the first woman artist to be represented in the collection of the National Museum of Ethiopia.

በኢትዮጵያ ያለውን የእለት ተእለት ኑሮ የሚያሳዩት የደስታ ሃጎስ ሥዕሎች ሴቶች የሚጋፈጡትን የሕይወት ትግል ወይም በትካዜ የተዋጡ ወንዶችን ያስቃኛሉ፡፡ በተጨማሪም ደስታ የአርምሞ ሕይወትን፣ የመሬት አቀማመጥን እና ረቂቅ ውሕዶችን ትስላለች፡፡ በ1969 [እ.ኤ.አ.] ከአዲስ አበባ የሥነ-ጥበብ ትምሕርት ቤት ስትመረቅ ያቀረበችው የሥዕል ኤግዚቢሽን እንዲህ አይነት ዝግጅት ለማዘጋጀት የመጀመሪያዋ ሴት ሰዓሊ ያደርጋታል፡፡ በታውዘንድ አክስ፣ ካሊፎርኒያ ከሚገኘው የካሊፎርኒያ ሉተራን ዩኒቨርሲቲ ሙሉ ነጻ የትምሕርት እድል አግኝታ የሥነ-ጥበብ የመጀመሪያ ዲግሪ አጠናቃለች፡፡ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ-መዘክር በሚገኙ የሥዕል ጥርቅሞች ስራዎቿን ለማበርከት የመጀመሪያዋ ሴት ሰዓሊ ናት፡፡

"Most of my works are semi-abstract, and I use Ethiopian landscapes and day-to-day life as my subject matter. Listening to music has always been a backdrop for my artistic temperament."

"አብዛኛዎቹ የእኔ ሥራዎች በከፊል ረቂቅ ሲሆኑ፣ የሥዕሎቼም አርዕስት የኢትዮጵያ የመሬት አቀማመጥ እና የእለት ተእለት ኑሮ ናቸው፡፡ ላለኝ የሥዕል ዝንባሌ መዚቃ ማድመጥ ምንጊዜም ድጋፍ ሲሰጠኝ ኖሯል፡፡"

VALERIE HAMMOND ቫለሪ ሃሞንድ

In her work, Valerie Hammond is drawn to the images and devotional qualities of church shrines, Asian art and Buddhist sculptures, objects that express intimacy and connection. In *Eather*, she combines hand gestures with the imagery of emotion and spirit, blending a tangible body feature with elusive qualities that help shape identity. Born in Santa Maria, California, Hammond received her master of fine arts from the University of California at Berkeley. She teaches printmaking and has had exhibitions in the U.S., Madrid, New Delhi and New Zealand.

ቫለሪ ሃሞንድ በምትሰራቸው ሥራዎች እንደሚታየው በአብያተክርስቲያናት መቅደሶች፣ በእሲያ ሥነ-ጥበብ እና የቀረበ ግንኙነትን እንዲሁም መግባባትን በተላበሱት የቡዲስት ቅርጻ ቅርጾች ትመሰጣለች፡፡ ኤኢተር በተባለው ሥራዋ በእጅ እንቅስቃሴ የሚገለጹ መልካም መልዕክቶችን ከምናባዊ ስሜት እና መንፈስ ጋር አዋሕዳለች፡፡ በዚህም መልኩ በቀላሉ ለመግለጽ የሚያስቸግሩ ነገር ግን ማንነትን የሚቀርጹ ምስጉን ባሕሪያትን ተጨባጭ ከሆነ አካላዊ ገጽታ ጋር ለማቀናጀት ችላለች፡፡ በሳንታ ማሪያ፣ ካሊፎርኒያ የተወለደችው ሃሞንድ በበርክሌይ ከሚገኘው የካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ በሥነ-ጥበብ የድሕረ ምረቃ ዲግሪዋን አግኝታለች፡ ፡ የሕትመት ትምሕርት የምታስተምር ከመሆኑም ባሻገር፣ ሥራዎቿን በአሜሪካ፣ በማድሪድ፣ በኒው ዴልሂ እና በኒው ዚላንድ ለዕይታ አቅርባለች፡፡

"Layering is an essential aspect of my work. I begin by collecting ferns and other organic materials, transforming them though drawing and the printmaking process, then creating images that marry the ferns to the images of the body. These images reflect the uniqueness of individual hands, as well as reveal the tracing of the spirit."

"ድርብርብ ቅርጽ መስራት የስራዬ ወሳኝ ክፍል ነው፡፡ የእጽዋትን አካላት እና ሴሎች አሰፈላጊ ተፈጥሯዊ ነገሮችን በማጠራቀም እጀምራለሁ፡ ፡ በሥዕል እና ሕትመት ከለወጥኳቸው በኋላ የእዕዋቱን አካላት ከሰውነት ምስሎች ጋር የሚያዋሕዱ ገጽታዎች እፈጥራለሁ፡፡ እነዚህ ምስሎች የተናጠል ልዩ መሆንን እጅች እና መንፈስን ፈልጎ ማግኘትን ያንጸባርቃሉ፡፡"

DRISCOLL HIXSON ድሪስኮል ሂክሰን

As a printmaker, Driscoll Hixson explores monoprinting, etching and woodblock, all printmaking methods that produce a single impression from a reprintable block. He is also a designer and incorporates a passion for typography into his commercial design work and printmaking. Born in Detroit, Michigan, Hixson earned a bachelor of fine arts and a master of fine arts from the University of Michigan, Ann Arbor. He is an assistant professor of graphic design at the University of Wisconsin, Madison, and has exhibited in the U.S., the Czech Republic and China.

በቀለም የሚሰሩ የጥበብ ሥራዎች ባለሙያ እንደመሆኑ መጠን፣ ድሪስኮል ሂክሰን ተመሳሳይ ቀለም ይጠቀማል፤ ቅርጽን በመጠቀም እና በእንጨት ላይ ቅርጽ በማውጣት አንድን ገጽታ ይፈጥራል፡፡ የተለያዩ የሕትመት ውጤቶችን ለማጣመር ሥራ ከፍተኛ ፍቅር ያለው በመሆኑ፣ ይህንን ሙያ ለማስታወቂያ ንድፍ እና የሕትመት ሥራዎች ይጠቀምባቸዋል፡፡ በዴትሮይት፣ ሚቺጋን የተወለደው ሂክሰን በአን አርበር ከሚገኘው ሚቺጋን ዩኒቨርሲቲ በሥነ-ጥበብ የመጀመሪያ እና የድሕረ ምረቃ ዲግሪ አግኝቷል፡፡ በዊስኮንሰን ዩኒቨርሲቲ፣ ማዲሰን የግራፊክ ዲዛይን ረዳት ፕሮፌሰር ነው፡፡ ስራዎቹንም በአሜሪካ፣ በቼክ ሪፑብሊክ እና በቻይና ለአይታ አቅርቧል፡፡

"Growing up surrounded by textiles, I learned the principles of design by escaping into and under my mother's sewing shop—the kitchen table. Traces of my past are interwoven from textile memories to the verdant countryside of my childhood home. Land, architecture, and narratives intersect through the structuring of fragmented letterforms, colors, and textures."

"በጨርቃ ጨርቅ ተከብቤ ያደግሁ በመሆኑ፣ የንድፍ አወጣጥን መርሆዎች የእናቴ የስፌት ቦታ በነበረው የማዕድ ቤት ጠረጼዛ ስር በመግባት እና በመደበቅ የንድፍ አወጣጥን መርሆዎች ተማርኩ፡፡ ቀደም ስላለው ዘመኔ ሳስብ፣ የጨርቃ ጨርቅ ንድፎች እና በልጅነት ዘመኔ ባደግሁበት ገጠራማ አካባቢ የነበረው የዕጽዋት ውበት እርስ በእርሳቸው ተሳስረው ይታዩኛል፡፡ የመሬት ገጽታ፣ ሥነ-ሕንጻ እና ትረካዎች በልዩ አጣጣል ተሰባጥረው በተጻፉ ፊደላት፣ በቀለማት እና ቅርጾች ውስጥ ተሳስረው ይታዩኛል፡፡"

BONNIE LEE HOLLAND ቦኒ ሊ ሆላንድ

Award-winning mixed-media artist Bonnie Lee Holland primarily exhibits paintings, textiles, hand scrolls, and installations. She uses her experience with animated film, dance, poetry, and narrative to convey concepts of transformation, metamorphosis, growth, internal and external journeys and non-static portraits.

ተሸላሚ እና የልዩ ልዩ መሳያ አርቲስት የሆነችው ቦኒ ሊ ሆላንድ በዋናነት በቀለም የተሳሉ ሥዕሎችን፣ ጨርቃጨርቆችን፣ የእጅ ብራናዎችን እና ሥዕላዊ መግለጫዎችን ለዕይታ ታቀርባለች፡፡ በካርቱን ፊልም፣ በዳንስ፣ በግጥም እና በትረካ ረገድ ያሏትን ልምዶች በመጠቀም፣ የለውጥን፣ ፈጣን የለውጥ ሂደቶችን፣ እድገትን፣ ውስጣዊ እና ውጫዊ ጉዞዎችን እና ተንቀሳቃሽ ሥዕሎችን ትስላለች፡፡

"I love the adventure and challenge of taking disparate elements and melding them into a cohesive whole through active engagement, a dialog process, and states of flow. Even when I start with a plan and research, my process always brings me to something new I didn't anticipate. Song: Time Echoes *is in part inspired by a quote from Rilke: 'Song is existence.' The painting's abstract images encompass time, landscape, history, architecture, textiles, artwork, and food, reflecting my exploration of Ethiopia's culture and traditions."*

"የወዳደቁ ነገሮችን በመጠቀም በትኩረት፣ በጥልቀት እና በሂደት ወደ አንድ ሙሉ ገጽታ ማምጣት አጅግ የሚያስደስተኝ የአዲስ ነገር ሙከራ እና ፈታኝ ሥራ ነው፡፡ እቅድ አውጥቼ እና በጥናት ላይ ተመርኩዤ ስራዬን ስጀምር እንኳን፣ ሁሌም ቢሆን የጀመርኩት ሥራ በሂደት ወደ አልጠበቅሁት ነገር ያደርሰኛል፡፡ ጊዜ ያስተጋባል በመባል የሚታወቀው ዘፈን የመነጨው ከገጣሚ ሪልኬ ዘፈን ሕያውነት ነው" ("ዝማሬ መኖር ነው") ከሚለው ጥቅስ ነው፡፡ ሥዕሎቼ ገጽታዎችን፣ ጊዜን፣ የመሬት አቀማመጥን፣ ታሪክን፣ ሥነ-ሕንጻን፣ ጨርቃ ጨርቅን፣ የሥነ-ጥበብ ሥራን እና ምግብን ያካተቱ ናቸው፡፡ እነርሱም በኢትዮጵያ ባሕል እና ልማድ ላይ ባለኝ እውቀት ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡"

RICHARD M. HUNT ሪቻርድ ኤም. ኸንት

Though Richard Hunt is best known for his public sculpture, usually welded bronze or steel, his works on paper reflect the same energy and vitality as his three-dimensional work. Central to all his work is a desire to blend the industrial and the organic, a unification of the modern and natural worlds. Hunt earned a bachelor's degree from the School of the Art Institute of Chicago. He has received numerous awards for his work and he is represented in the permanent collections of museums throughout the world. In 1971, he became the first black artist to have a solo exhibition at the Museum of Modern Art in New York City.

ሪቻርድ ኸንት በይበልጥ የሚታወቀው በአብዛኛው በመዳብ ወይም በብረት ብየዳ በሚሠራቸው ሕዝባዊ የቅርጻ ቅርጽ ስራዎቹ ቢሆንም፣ እንደ ባለሦስት ጎን የጥበብ ሥራዎቹ ሁሉ በተመሳሳይ ጥንቃሬና ብቃት በወረቀት ላይም ይሠራል፡ ፡ የሥራዎቹ ማዕከላዊ ነጥብም የዘመናዊ እና ተፈጥራዊ ጥምረት ጥንካሬና ሰው ሠራሽ ነገሮችን ማዋሃድ ነው፡፡ ኸንት ከቺካጎ የሥነ-ጥበብ ትምሕርት ቤት ተቋም የመጀመሪያ ዲግሪን አገኘ፡፡ በሥራዎቹም በርካታ ሽልማቶች አግኝቷል፡፡ በአለም ዙሪያ ቋሚ በሆኑ ቤተ-መዘክሮች ሥራዎቹ ይገኛሉ፡ ፡ በ1971 [እ.ኤ.አ.] በኒው ዮርክ ከተማ ዘመናዊ የሥነ ጥበብ ቤተ መዘክር የተናጠል ኤግዚቢሽን ለማቅረብ የመጀመሪያው ጥቁር አርቲስት ነው፡፡

"I like to think that within the work …there is a resolution of the tension between the sense of freedom one has in contemplating nature and the sometimes restrictive, closed feeling engendered by the rigors of the city, the rigors of the industrial environment."

"በሥራው ውስጥ ..... አንድ ሰው ስለተፈጥሮ በሚያስብበት ጊዜ በሚያገኘው ነጻነት እና በከተማ ኑሮ፣ በኢንዱስትሪ ሁኔታ ጥብቅነት ምክንያት በሚፈጠረው ገደብ በበዛበት በከተማ ጥንካሬ፣ የታጠረ ስሜት መካከል ባለው ውጥረት ላይ ሕይወት ይዘራል ብዬ ማሰብ አፈልጋለሁ፡፡"

LINDA INGRAHAM ሊንዳ ኢንግራሃም

Linda Ingraham's photo constructions capture ideas or emotions with a single haunting image, or a juxtaposition of image and object, which translate to visual metaphors for fear, hope and desire. Her pigment-printed prints reveal the patterns and intricacies of nature, elevating them to iconic status to emphasize the sacredness and beauty of life. Ingraham attended the University of New Mexico and received degrees in fine arts, art history, and French from New Mexico State University. Museums and galleries throughout the U.S. and abroad have exhibited her work and she is represented in museum and private collections worldwide.

የሊንዳ ኢንግራሃም የፎቶ ሥራዎች አንድን ምስል በተደጋጋሚ ወደ አዕምሮ የሚያመጡ ሃሳቦች እና ስሜት ያሉባቸው ናቸው፡፡ በሌላ አባባል አንድ ምስል ወይም ግዑዝ ነገር አጠገብ ላጠገብ ተቀምጦ የምናይበት እና የፍርሃትን፣ የተስፋን እና የፍላጎትን ጥልቅ ሃሳብ በአይናችን የምንቃኝበት ነው፡፡ የሥራው ቀለማት የተፈጥሮን አኳኋን እና ውስብስብ ባሕርይ ምስጢራዊ በሆነ አገላለጽ የምናይባቸው ሲሆን፣ ለሕይወት ቅዱስነት እና ውበት ልዩ ዋጋ ተሰጥቶ እናያለን፡፡ ኢንግራሃም በኒው ሜክሲኮ ዩኒቨርሲቲ ትምሕርቷን ተከታትላ ከኒው ሜክሲኮ ስቴት ዩኒቨርሲቲ ደግሞ በሥነ-ጥበብ፣ በሥነ-ጥበብ ታሪክ እና በፈረንሳይ ቋንቋ ዲግሪዎች አግኝታለች፡ ፡ በአሜሪካ እና በመላው ዓለም የሚገኙ ቤተ መዘክሮች ሠገነቶች ሥራዎቿን ለእይታ ያቀረቡ ሲሆን፣ በዓለም ዙሪያ ደግሞ በቤተመዘክሮች እና በግል ጥርቅሞች ዘንድ የእርሷ ሥራዎች ይገኛሉ፡፡

"I am drawn to beautiful things…but beauty that reaches beyond the eyes and into the soul, the poignant beauty of spirituality, loss, fragility, and hope. These are the themes that weave a common thread through my work, using nature as metaphor to explore the human psyche."

"ውብ ነገሮች ይመስጡኛል ..... ይህንን ስል ከኢይን ኢይታ ውጭ የሆኑ እና ወደ ነፍስ የሚጠልቁትን ማለቴ ነው፣ የመንፈሳዊነት፣ የኦጦት፣ የደካማነት እና የተስፋ ውበቶች ይስቡኛል፡፡ በስራዎቼ ውስጥ የሚያስተሳስር ክር የሚፈጥሩት እነዚህ ቁም ነገሮች ናቸው፡፡ የሰውን ልጅ ሥነ-ልቦናም ተፈጥሮን እንደማነጻጸሪያ በመጠቀም አሳያለሁ፡፡"

AGNES JACOBS አግነስ ጃኮብስ

Born in Budapest, Hungary, Agnes Jacobs has explored diverse artistic media including three-dimensional wall constructions and brightly colored monotype prints. Always present in her work is movement, freedom of mark and strong linearity. Jacobs studied at the Art Students League in New York City and received a degree in art history at Barnard College, Columbia University, New York City, and a master of fine arts at George Washington University, Washington, D.C. She has received many commissions for her work and she is represented in many collections including the National Museum of Women in the Arts, Washington, D.C.

በቡዳፔስት፣ ሃንጋሪ የተወለደችው አግነስ ጃኮብስ የተለያዩ የሥዕል መሳያዎች ላይ የሰራች ሲሆን፣ ከነዚህም መካከል ባለሶስት ገጽታ የግርግዳ ግንባታ እና ደማቅ አንድ ወጥ ቀለም ያላቸው ሥዕሎች ይገኙባቸዋል፡፡ በሥራዎቿ ላይ ሁልጊዜም እንቅስቃሴ፣ ነጻ አሳሳል እና ጠንካራ ባለ አንድ አቅጣጫ ገጽታ ይንጸባረቃሉ፡፡ ጃኮብስ በኒው ዮርክ ከተማ በአርት ስቱደንትስ ሊግ ትምሕርቷን ተከታትላለች፡፡ በኒው ዮርክ ከተማ ከሚገኘው ኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ፣ በርናርድ ኮሌጅ በሥነ-ጥበብ ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪ እና በዋሽንግተን ዲ.ሲ. ከሚገኘው ጆርጅ ዋሽንግተን ዩኒቨርሲቲ በሥነ-ጥበብ የድሕረ ምረቃ ዲግሪዋን አግኝታለች፡፡ በሥራዋ በርካታ ኃላፊነቶች ላይ ሠርታለች፤ በዋሽንግተን ዲ.ሲ፣ በሥነ-ጥበብ ሴቶች ብሔራዊ ቤተ-መዘክር እና በሌሎችም ጥርቅሞች ውስጥ የእርሷ የጥበብ ሥራዎች ይገኛሉ፡፡

"A sense of play is always apparent in my work. I 'play' with the shapes, colors, patterns and linear elements until I reach a point in which the whole seems ready to unravel. Then, at the last moment I add an element that creates harmony, and then 'rescuing' it is very exciting for me."

"ሁሌም በሥራዎቼ ጨዋታ መሰል ነገር አለ፡፡ በጠቅላላው ሲታይ አንዳች ትርጉም የሚሰጥ ነገር እስካገኝ ድረስ በቅርጾች፣ በቀለማት፣ በአጣጣል ዘይቤ እና በባለ አንድ ገጽታ የሥራዎቼ ክፍሎች "እጫወታለሁ"፡፡ ከዚያም በኋላ በመጨረሻው ጊዜ በእነዚያ ነገሮች መካከል የሰመረ መስተጋብር የሚፈጥርልኝ ነገር ስጨምር እጅግ ደስ ይለኛል፡፡"

BARBARA KERNE ባርባራ ኬርኔ

In Barbara Kerne's woodcuts, images from the natural world merge with mythical narratives and the symbols and language of distant cultures and times. She sees her work as a doorway to a space where mysteries are unlocked, and a pathway to acquiring a spiritual knowledge of place. Kerne is professor emeritus at Montgomery College, Maryland, and has work in collections including the Corcoran Gallery of Art, Washington, D.C.; the Library of Congress, Washington, D.C., and the Portland Art Museum, Portland, Oregon.

በባርባራ ኬርኔ የእንጨት ቁርጥራጭ ቅርጾች፣ ምስጢራዊ መልዕክት ያላቸው ምስሎች ከተፈጥሯዊው አለም፣ ከተለያዩ ባሕሎች እና ቋንቋዎች እንዲሁም ከጊዜያት ጋር ትስስር ይፈጥራሉ፡፡ ሥራዎቿን ሚስጥሮች ወደሚፈቱበት ስፍራ እና መንፈሣዊ ዕውቀት ወደሚገኝበት ቦታ እንደሚወስድ በር ታያቸዋለች፡፡ ኬርኔ በሜሪላንድ በሚገኘው ሞንትጎመሪ ኮሌጅ ተጣሪ የክብር ፕሮፌሰር ስትሆን በዋሽንግተን ዲ.ሲ. በኮርኮራን የሥነ ጥበብ ሠገነት፣ በዋሽንግተን ዲ.ሲ. የኮንግሬስ ቤተ-መጻሕፍት እና በፖርትላንድ፣ ኦሪገን በሚገኘው ፖርትላንድ የሥነ-ጥበብ ቤተ-መዘክር እንዲሁም በሌሎችም የጥበብ ሥራ ጥርቅሞች ውስጥ የእርሷም ሥራዎች ይገኛሉ፡፡

"My art reflects my life and the life around me. Landscape, myth and memory are sources. Daily walks along the river keep me close: touching and tasting, seeing and smelling ever-changing nature. I walk in woods, mountains and fields, by river and sea, seeking the living places on the earth—sacred spaces where communication with nature transcends the mundane, satisfying the longings of the soul."

"የጥበብ ሥራዎቼ የእኔ እና በዙሪያዬ ያለው ሕይወት ነጸብራቆች ናቸው፡፡ ምንጮቻቸውም የመሬት አቀማመጥ፣ አፈ-ታሪክ እና ትውስታዎቼ ናቸው፡፡ በወንዙ ዳርቻ በየእለቱ የማደርገው የእግር ጉዞ ከእነርሱ ጋር በቅርበት እንድገናኝ ያደርገኛል፤ በየጊዜው የሚለወጠውን ተፈጥሮ እንድዳስስ፣ እንድቀምስ፣ እንዳይ እና እንዳሸት ያደርገኛል፡፡ በጫካዎች፣ በተራራ እና በመስክ ላይ፤ በወንዝ እና በባሕር ዳርቻ የእግር ጉዞ አደርጋለሁ፡፡ ይህም በመደበኛ ሕይወት ውስጥ ካለው እጅግ በላቀ ሁኔታ ከተፈጥሮ ጋር ያለን ግንኙነት እውን የሚሆንበት ቅዱስ ቦታ ነው፣ የነፍሳችንም ጥማት ይረካል፡፡"

WOSENE WORKE KOSROF ወሰኔ ወርቄ ኮስሮፍ

Wosene Worke Kosrof uses the aesthetic potential of Amharic as the major compositional element in his paintings. Calligraphic forms are broken apart, abstracted, and reconfigured to create a new visual language. Wosene's compositions draw upon his Ethiopian heritage while incorporating his experiences as an expatriate living in the U.S. He earned a bachelor of fine arts from the Addis Ababa Fine Arts School and a master of fine arts from Howard University in Washington, D.C. He has had solo and group exhibitions in the U.S., the U.K., Europe and Africa.

ወሰኔ ወርቄ ኮስሮፍ በሥዕል ቅቦች ሥራዎቹ ውስጥ የአማርኛን እምቅ ውበት እንደዋነኛ ግብዓት ይጠቀምበታል፡ ፡ የጽሁፍ አጣጣል አይነቶች ተሰባብረው፣ ረቂቅ ተደርገው እና በድጋሚ ተቀናጅተው አዲስ የሚታይ ቋንቋ ይፈጥራሉ፡ ፡ የወሰኔ የሥዕል ሥራዎች በዋናነት የኢትዮጵያን ቅርስ የሚጠቀም ሲሆን፣ በአሜሪካ ነዋሪ እንደመሆኑ መጠን ከዚህ ጋር በተያያዘ ያገኘውን ልምድ በሥራዎቹ ውስጥ ያካትታል፡ ፡ በሥነ-ጥበብ የመጀመሪያ ዲግሪውን ከአዲስ አበባ የሥነ-ጥበብ ትምሕርት ቤት አገኘ፤ በዋሽንግተን ዲ.ሲ. ከሚገኘው ሆዋርድ ዩኒቨርሲቲ ደግሞ በሥነ-ጥበብ የድሕረ ምረቃ ዲግሪውን ይዟል፡፡ በአሜሪካ፣ በእንግሊዝ፣ በአውሮፓ እና በአፍሪካ በተናጠል እና በቡድን ኤግዚቢሽኖች ሥራዎቹን ለዕይታ አቅርቧል፡፡

"I 'dialogue' with the (language) symbols as they emerge, working them up with colors and layering them with wet and dried acrylic paint. The canvas becomes an enlivened space, with texture and depth, and the symbols often surprise me with their unexpected transformations. My painting process is an intense interplay of intention and accident, curiosity and discovery."

"የ(ቋንቋው) ምልክቶች እየታዩ በመጡ ጊዜ ከእነርሱ ጋር እነጋገራለሁ፤ በቀለማት፣ በእርጥብ እና ደረቅ የአክሪሊክ ቅብ እየደራረብኳቸው አዘጋጃቸዋለሁ፡፡ ሸራውም ሸካራ መሰል ገጽታ እና ጥልቀትን በማካተት አስደሳች ይሆናል፡፡ ምልክቶቹንም ሳያቸው በማያሳዩት ያልተጠበቀ ለውጥ ድንቅ ይሆኑብኛል፡፡ የሥራውም ሂደት ሆን ተብሎ በሚደረግ እና በአጋጣሚ በሚገኝ ውጤት መካከል ያለ ልውውጥ እና አጋጣሚ ነው ። የማወቅ ጉጉት እና አዲስ ግኝትም የእርሱ አካላት ናቸው፡፡"

YOSEF LULE ዮሴፍ ሉሌ

Yosef Lule's oil paintings, originally figurative, have gradually become abstract. The roots of his style come from observing the Addis Ababa mountains, and images such as colorful clothes drying in the grass. Yosef graduated from Addis Ababa Fine Arts School and is part of the Habesha Art Studio in Addis Ababa, a small cooperative studio and exhibition space dedicated to promoting contemporary Ethiopian art. His work has been in solo and group exhibitions in Ethiopia, Switzerland and France.

የዮሴፍ ሉሌ በዘይት ቀለም የሚሰሩ ሥዕሎች ቀደም ሲል ምሳሌያዊ የነበሩ ሲሆን፣ በሂደት ረቂቅ እየሆኑ መጥተዋል፡ ፡ የአሳሳል ዘይቤው ዋነኛ መነሻዎች የአዲስ አበባ ተራሮች እይታ እንዲሁም በሳር ላይ ተሰጥተው የሚደርቁ አልባሳት እና የመሳሰሉ ምልከታዎች ናቸው፡፡ ዮሴፍ ከአዲስ አበባ የሥነ-ጥበብ ትምሕርት ቤት ተመርቋል፤ በአዲስ አበባ የአበሻ የሥነ-ጥበብ ስቱዲዮ አባልም ነው፡፡ ይህ ስቱዲዮ በሕብረት ሥራ መልክ የተቋቋመ እና የኢትዮጵያን ዘመናዊ ሥዕል ለማበረታታት የታለመ አነስተኛ የኤግዚቢሽን ስፍራ ነው፡፡ ሥራዎቹ በኢትዮጵያ፣ በስዊዘርላንድ እና በፈረንሳይ በተናጠል እና በቡድን ኤግዝቢሽኖች ለእይታ ቀርበዋል፡፡

"My inspiration is coming from what I see…and mainly feel daily (and from) my travels in Egypt, Zanzibar, Spain and France. I believe that I have to bring happiness through my paintings, and not sadness."

"ተነሳሳሽነቴ የሚመነጨው ከማየው ነገር ነው .... በየእለቱ ከማየው እና ወደ ግብጽ፣ ዛንዚባር፣ ስፔን እና ፈረንሳይ በተጓዝኩባቸው ጊዜያት ከተመለከትኩአቸው እንዲሁም በሥዕሎቼ ደስታን እንጂ ሐዘንን ማምጣት አለብኝ ብዬ አላምንም፡፡"

ERMIAS MAZENGIA ኤርሚያስ ማዘንጊያ

Ermias Mazengia's distinct visual language grew from an exploration of forms, patterns and brush strokes that would give artistic expression to the emotions that inspired his work. Ermias studied with Mezgebu Tessema at Addis Ababa School of Fine Arts and Design and later attended an extended residency in South Africa. He has exhibited his work in solo exhibitions at the Tewanney Studio, Addis Ababa; the Goethe Institute, Addis Ababa; the Alliance Ethio-Francaise, Addis Ababa; the Greatmore Studio in Cape Town, South Africa; and the LeLa Art Gallery, Addis Ababa, and in numerous group exhibitions in Ethiopia and abroad.

የኤርሚያስ ማዘንጊያ ለየት ያለ የእይታ ቋንቋ የጎለበተው ፎርሞችን፣ የአሳሳል ዘይቤን እና የብሩሽን አጣጣል በጥንቃቄ በመፈተሽ ነው፡፡ በዚህም ሂደት ለሥራው መነሳሳት ለሆኑት ስሜቶች ጥበብ የተሞላበት አገላለጽ ያላበሳል፡፡ ኤርሚያስ ከመዝገቡ ተሰማ ጋር በአዲስ አበባ የሥነ-ጥበብ እና ዲዛይን ትምሕርት ቤት እና ከዚያም በማስከተል በደቡብ አፍሪካ ቆይታ ትምሕርቱን ተከታተለ፡፡ ሥራዎቹን በአዲስ አበባ በሚገኙት ተዋኔ ስቱዲዮ፣ ጎተ ተቋም፤ አሊያንስ ኢትዮ ፍራንሴስ፣ በኬፕታውን በግሬትሞር ስቱዲዮ እና በአዲስ አበባ በሌላ የስሥነ-ጥበብ ሠገነት፣ በኢትዮጵያ እንዲሁም በውጭ ሃገራት በተናጠል እና በቡድን ኤግዚቢሽኖች ለእይታ አብቅቷል፡፡

"I never think about a painting. A painting is not an idea, it's like swimming through the spiritual and the scientific realities of existence. My art is a contemporary reflection of the universe…."

"ሥዕል ስለመሳል አላስብም፡፡ ሥዕል መሳል የሃሳብ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይልቁንም በቁስ አካል መንፈሳዊ እና ሳይንሳዊ እውነታዎች ውስጥ መዋኘት ማለት ነው፡፡ የእኔ ሥዕሎች የዓለም ዘመናዊ ነጸብራቆች ናቸው……፡፡"

BEKELE MEKONNEN በቀለ መኮንን

Bekele Mekonnen's social commentary on conditions in modern Ethiopia is presented variously through irony, humor, and metaphor. Frustrated by persistent hunger in his country, Bekele chooses objects representing food production and alters them to convey futility, such as a plough with its tip curled up. Salvaged, cut, assembled and glued, his materials bend and contort to reflect brutal conditions still evident in Ethiopia. Bekele graduated from the Addis Ababa Fine Arts School and earned a master of fine arts in sculpture from Moscow State Academic Institute of Fine Arts. He later returned to Addis Ababa to teach at the Fine Arts School and serve as director when the school integrated with Addis Ababa University as the School of Fine Arts and Design. Bekele lectures on sculpture and art history and has exhibited in the U.S., Europe and Africa.

በቀለ መኮንን በዘመናዊቷ ኢትዮጵያ ላይ የሰጠው ማሕበራዊ አስተያየት በአሽሙር፣ በቀልድ እና አንድን ነገር በሌላ በመወከል በሰፊው ቀርቧል፡፡ በሃገሪቱ በቀጣይነት በሚያጋጥመው ረሃብ በመከፋት የምግብ እህል ምርትን የሚወክሉ ነገሮችን በሥዕሉ ለማካተት ቢመርጥም የምርቱ ነገር ውጤት አልባ መሆኑን ለማሳየት ለምሳሌ ጫፉ ወደላይ የታጠፈ ማረሻን ያሳየናል፡፡ ቁሳቁሶቹ የተጎሳቆሉ፣ የተቆራረጡ፣ በድጋሚ የተገጣጠሙ እና የተጣበቁ በመሆናቸው ተጣጥፈው እና ከመደበኛው ቅርጽ ውጭ ሆነው በአሁኑ ጊዜም ቢሆን በኢትዮጵያ ያለውን አስከፊ ሁኔታ ያሳያሉ፡፡ ከአዲስ አበባ የሥነ-ጥበብ ትምሕርት ቤት የተመረቀው በቀለ ከሞስኮ ስቴት አካዳሚክ የሥነ-ጥበብ ተቋም በቅርጻ ቅርጽ የድሕረ ምረቃ ዲግሪውን አግኝቷል፡ ፡ በማስከተልም በሥነ-ጥበብ ትምሕርት ቤት ለማስተማር እና ትምሕርት ቤቱ የሥነ-ጥበብ እና ዲዛይን ትምሕርት ቤት በሚል ስያሜ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በተቀላቀለበት ጊዜ በዳይሬክተርነት ለማገልገል ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ፡ ፡ በቀለ የቅርጻ ቅርጽ ትምሕርት እና የሥነ-ጥበብ ታሪክ መምሕር ነው፡፡ ሥራዎቹን በአሜሪካ፣ በአውሮፓ እና በአፍሪካ ለዕይታ አቅርቧል፡፡

"I have to transform everything into art."

"ሁሉንም ነገር ወደ ሥነ-ጥበብ መለወጥ አለብኝ"

JULIE MEHRETU ጁሊ ምሕረቱ

